# የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ነጻነትና ዓለም አቀፍ ህግጋት

ስለ ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች እንቅስቃሴ ሲወሳ በብዛት የሚነሳው አንደኛው አቢይ ጥያቄ እነዚህ ተቋማት ስራቸውን ምን ያህል በነጻነት ይሰራሉ የሚለው ነው። ይህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ የሚነሳበትና ዋነኛ ጥያቄ የሆነበት ምክንያትም ተቋማቱ ስራቸውን በገለልተኝነትና በውጤታማነት ለመስራት የሚያግዱዋቸው ውጫዊ ተጽዕኖዎች በመንግስት ውስጥ ባሉት ህግ አውጪና ህግ አስፈጻሚ አካላት ሊደርሱባቸው የሚችልበት እድልና ሁኔታ ስላለ ነው።

ነባራዊው ሁኔታ ሲታይ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የሀገራቸው መንግስት አካል በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ነጻ መሆን አይችሉም። ይሁንና በዚህ ሁኔታ ውስጥም ቢሆን የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ከተጽዕኖዎቹ (በአንጻራዊነት) ነጻ ሆነው ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማድረግ በዓለም አቀፉ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ተቋማት ማህበር (INTOSAI) እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በተደረጉ ጥረቶች የተቋማቱን ነጻነት አስመልክቶ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የህግ ማእቀፎች በየወቅቱ ወጥተዋል። በዚህ ረገድ የሚጠቀሱት የህግ ማዕቀፎች ውስጥ የሊማ ዲክላሬሽን፣ የሜክሲኮ ዲክላሬሽን እና የተባበሩት መንግስታት ሪዞሊሽን ተጠቃሽ ናቸው።

የሊማ ዲክላሬሽን (the Lima Declaration of Guidelines on Auditing Percepts) እ.ኤ.አ. በ1977 በፔሩ ዋና ከተማ ሊማ ላይ በተደረገው 9ኛው የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ዓለም አቀፍ ጉባኤ (INCOSAI) ላይ የጸደቀ ህግ ነው። የዚህ ዲክላሬሽን ዋነኛ አላማ ነጻና ውጤታማ የመንግስት ኦዲት እንዲኖር ማድረግ ነው። መነሻ ሀሳቡም ነጻ ያልሆነ ተቋም የሚጠበቅበትን ያህል ሊሰራ አይችልም የሚል ሲሆን ነጻና ውጤታማ የመንግስት ኦዲት እንዲኖር የዋና ኦዲት መ/ቤቶች የስራ እና ተቋማዊ ነጻነት /functional and organizational independence እንዲኖራቸው ማድረግ ብሎም የህግ የበላይነትንና ዲሞክራሲን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ይላል።

ዲክላሬሽኑ ነጻ የመንግስት ኦዲትን ለማምጣት ሲባል በህገመንግስትና በሌሎች ዝርዝር ህጎች ውስጥ ሊካተቱ ይገባል ያላቸውን ጉዳዮች የያዘ ሲሆን አሁን ላለው የመንግስት ኦዲት ስራ የነጻነት የውል/የስምምነት ሰነድ/magna carta ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

የሊማ ዲክላሬሽን የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች መቋቋም እንዲሁም ያላቸው ነጻነት በህገመንግስት ውስጥ ተካቶ መደንገግ እንዳለበት ዝርዝር ጉዳዮችም በሌሎች ህጎች ሊደነገጉ እንደሚችሉ በአጽንኦት ይገልጻል። የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በነጻነታቸውና በተሰጣቸው ስልጣን ላይ ከሚደረግ ማናቸውም ጣልቃገብነት የሚጠበቁበት በቂ ህጋዊ ከለላ ሊደረግላቸው እንደሚገባም ያስገነዝባል። በተቋማቱ ውሳኔ የሚሰጡ የበላይ አመራሮች የስራ ነጻነትም እንደዚሁ ሊጠበቅና ይህም በህገመንግስቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባም ይገልጻል። የኦዲት ባለሙያዎችም ኦዲት በሚያደረጉዋቸው ተቋማት ተጽዕኖ ሊያድርባቸውና በነርሱም ላይ ጥገኛ ሊሆኑ እንደማይገባም ያስረዳል። በፋይናንስ በኩልም የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ለስራቸው አስፈላጊው

ፋይናንስ ሊመደብላቸው እንደሚገባና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙትም የሀገሪቱን በጀት ላይ ውሳኔ ለሚያስተላልፈው የመንግስት አካል የፋይናንስ ጥያቄያቸውን በቀጥታ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይገልጻል፡፡

የሊማ ዲክላሬሽን የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የፓርላማው ወኪል /agent/ ሆነው ሲሰሩና ፓርላማው የሚያዛቸውን ኦዲቶች ሲያከናውኑም እንኳ በራሳቸው የመንቀሳቀስና ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ከፍተኛ ነጻነት ያላቸው መሆኑ በህገ-መንግስትና በሌሎች ህጎች የተረጋገጠ መሆኑን ያስረዳል፡፡

የሜክሲኮ ዲክላሬሽን (Mexico Declaration on SAI Independence) በሊማ ዲክላሬሽን ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦችን አጽንኦት ሰጥቶ በመውሰድ እንዲሁም በደቡብ ኮርያ ዋና ከተማ ሴኡል በተደረገው 17ኛው የዓለም አቀፉ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ማህበር ጉባኤ የተወሰኑ ጉዳዮችን በማካተት እ.ኤ.አ. በ2007 በሜክሲኮ የጸደቀ ህግ ነው፡፡ ዲክላሬሽኑ ከዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ነጻነት ጋር የተያያዙ ስምንት ዋና ዋና መርሆዎችን የያዘ ሲሆን በአሁኑ ወቅት እነዚህ መርሆዎች የኦዲት ተቋማትን ነጻነት የሚገለጹባቸው ስምንት ምሰሶዎች እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

መርሆዎቹ በጥቅሉ ሲታዩ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ነጻነት በህገመንግስቱና በሌሎች ህጎች ውስጥ በግልጽ እንዲደነገግ ከማድረግ፤ ተቋማቱ አስፈላጊው የሰው ሀይል፣ ቁሳቁስና ገንዘብ እንዲኖራቸውና እነርሱንም ከመንግስት አካላት ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ከማድረግ፤ የተቋማቱ የበላይ የስራ ኃላፊዎች የስራ ዋስትናና ያለመከሰስ መብት /tenure and legal immunitiy/ ኖሯቸው ስራቸውን በነጻነት እንዲሰሩ ከማስቻል፤ ተቋማቱ በቂና ሰፊ ስልጣን /sufficiently broad mandate/ እንዲኖራቸው፣ በሚሰሩት ስራና በሚሰሩበት መንገድ እንዲሁም ራሳቸውን በሚያስተዳድሩበት አግባብ ላይ የመወሰን ነጻነት እንዲጎናጸፉና በዚህ ረገድ ከህግ አውጪውም ሆነ ከህግ አስፈጻሚው በኩል ከሚመጣባቸው መመሪያና ጣልቃ ገብነት/direction and interference እንዲጠበቁ ከማድረግ፤ ተቋማቱ ለስራቸው አስፈላጊ የሆነ ወቅታዊ፣ ያልተገደበ፣ ቀጥተኛ/direct ሙሉ መረጃ በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያስችል በቂ ስልጣን እንዲኖራቸው ከማድረግ፤ የኦዲት ሪፖርታቸውን ለማቅረብ ገደብ እንዳይደረግባቸው ከማድረግ፤ የኦዲት ሪፖርታቸውን ይዘት፣ ሪፖርቱን የሚያቀርቡበትን ጊዜ /timing፣ ሪፖርቱን በይፋ ለማውጣትና /publish ለማሰራጨት ያላቸውን ነጻነት ከማረጋገጥ እንዲሁም ለኦዲት ተደራጊ ተቋማት በሰጡት የማሻሻያ ሀሳብ /observation and recommendations መሰረት እርምጃ መወሰዱን የሚያረጋግጡበት ነጻ አሰራር /independent procedure ያላቸው መሆኑን ከማረጋገጥ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

እ.ኤ.አ በዲሴምበር 21 2011 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ነጻነት ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብና ዓለም አቀፉ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ማህበር የመንግስት ፋይናንስ ግልጽነት እንዲሰፍንበት እያደረገ ያለውን ጥረት በመደገፍ Promoting the efficiency, accountability,effectiveness and transparency of public administration by strengthening supreme audit institutions በሚል ርዕስ የውሳኔ ሀሳብ/resolution አስተላልፏል፡፡ የውሳኔ ሀሳቡ የኦዲት ተቋማትን

ነጻነት ለማጎልበት ያለመ ሲሆን የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ኃላፊነታቸውን ገለልተኛና ውጤታማ በሆነ አግባብ ማከናወን የሚችሉት በነጻነት ሲንቀሳቀሱ ብቻ እንደሆነ እውቅና ሰጥቷል። እንደዚሁም ተቋማቱ በህዝብ አስተዳደር ውስጥ የላቀ አፈጻጸምን፣ ተጠያቂነትን፣ ውጤታማነትነንና ግልጽነትን ለማስፈን ጠቃሚ ሚና እንዳላቸውና ይህም ለሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ግቦች መሳካት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ግንዛቤ ውስጥ አስገብቷል። በዚህም ምክንያት የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት በሊማና በሜክሲኮ ዲክላሬሽኖች ውስጥ የተካተቱትን መርሆች ከየራሳቸው ሀገራዊ ተቋማዊ አወቃቀር /national institutional structures ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲተገብሯው በውሳኔ ሀሳቡ ያበረታታል።

የመረጃ ምንጮች-


- Mexico Declaration on SAI Independence, ISSAI 10, AFROSAI
- The Lima Declaration,ISSAI 1, AFROSAI
- UN Resolution on the Independence of Supreme Audit Institutions (www.nik.gov.pl/en/news/un-resolution-on-the-independence-of-supreme-audit-institutions.html)
- United Nations General Assembly Resolution A/66/209
- intosai.org/fileadmin/downloads/downloads/4_documents/Folder_Englisch_2012.pdf)